አባ መቃርስ

ትዕይንት ፩

(መጋረጃ ሲከፈት አባ መቃርስ ብቻቸውን ይታያሉ።ድንገት ሳጥናኤል ሲያልፍ ያዩታል።)

አባ መቃርስ፡- አንተ እርኩስ መንፈስ እነሆ በእግዚአብሔር ስም ይገሥሃለሁ እንዳትንቀሳቀስ! ለመሆኑ ከየት ነው የምትመጣው?

ሳጥናኤል፡- በረሀ ላይ ያሉትን መነኮሳት እየተፈታተንኩ ነው፡፡ ከዛው ነው የምመጣው።

አባ መቃርስ፡- አንተ ዲያቢሎስ አንተ ክፉ በበረሃ ካሉት መነኮሳት ጋር በምታደርገው ውጊያ ስራህ እንዴት ነው?

ሳጥናኤል፡- በጣም መጥፎ ነው፡፡ ምንም እንኳን መነኮሳቱን ክፉ ኃጥያት እንዲሰሩ ባሳስባቸውም ሁሉም ያሳሰብኳቸውን ኃጥያት ለንሰሐ አባታቸው ይናገራሉ፡፡ አንዱ ግን ለንሰሐ አባቱ ስለማይናገር ከኔ ጋር ተወዳጅቷል። በጣም ደስ እያሰኘኝ ነው።

አባ መቃርስ፡- አንተ ርኩስ አንተ አስመሳይ ዘላለምህን ትዕቢተኛ ሀሰተኛ ቅናተኛ የተጠላህና የተዋረድክ ነህ፡፡

ሳጥናኤል፡- እና እንዲህ ካላደረክ ምኑን ኖርኩት? ሰዉ ሁላ መንግስተ ሰማያት ሊወርስ? አይሆንም

አባ መቃርስ፡- ክፉ ነፍሰ ገዳይ እውነት እንዲሰማ የማትሻ ለጥፋት አነሳሽ ጌታን እንኳን ያልፈራህ ፈታኝ ነህ፡፡ መልካምን ወደ ክፉ የምትለውጥ ለክፋት የምታነሳሳና የምትመራ አታላይ አስመሳይ ከበነ የምታዘገይ እንቅፋት ነህ፡፡ በምትሃት ተዓምር እያደረግህ ነገር የምታባብስ ሰዎችን በሕመም የምታሰቃይ ነህ፡፡ አሁን በመስቀሉ ሳላስርህ ካጠገቤ ራቅ፡፡ (ሰይጣን ይሰወራል። ከጥቂት ዝምታ በኋላ) አዎን ያን የተሳሳተ መነኩሴ ማግኘት አለብኝ። አሁኑኑ መሄድ አለብኝ።(ተነስተው ይሄዳሉ።)

ትዕይንት ፪

መነኩሴ፡- (መነኩሴው መጋረጃ ሲከፈት ቁጭ ብለው የጸሎት መጽሐፍ ያነባሉ። በድንገት ተመናጭቀው የጸሎት መጽሐፋቸውን ያስቀምጡና) ቆይ ለምንድን ነው? ኸረ ለምንድን ነው? . . . ኡፍፍ . . . ሁል ጊዜ ይሄ የራሴው ስጋ የሚፈታተነኝ ለምንድን ነው? እስከ መቼ ነው? ዘወትር ደካማ ሆኜ ቆይ ... ባንድ በኩል ወደ እግዚአብሔር መቅረብን እየፈለግኩ ... እንደገና ደግሞ የስጋዬን ፍላጎት ለማሟላት እጥራለሁ፡፡ (ተንበርክኮ) ጌታዬ ሆይ እባክህ ልቤን አጠንክረህ ለሰይጣን ምክር ጆርባዬን እንድሰጥ አድርገኝ፡፡ እባክህ አምላኬ ኃጥያትን እንዳልሰራ ቅዱስ ፍቃድህ ይሁንልኝ፡፡ (ተነስቶ የሹፈት ሳቅ በማሰማት) ለነገሩ በአፌ ጌታዬን እያመንኩ በተግባሬ አስቀይመዋለሁ፡፡ ፍላጎቴ ሁሉ የአፌ እንጂ የልቤ አልሆን ብሎኛል፡፡ አቤ...ት መች ይሆን እንደ ሐዋርያቱ የምጸናው፣ መች ይሆን ቅዱስ ጳውሎስን የምመስለው፣ መቼስ ነው እንደ አቡነ ተክለሃይማኖት የምጠነክረው ... መልሱልኛ ... አዋን መልሱልኝ ... ለነገሩ ማን ይመልስ ሁሉም የስጋውን ጥያቄ እንጅ የነፍሱን አይመልስም፡፡ በዚህች ምድር ላይ በድኖች እንጅ ህያዋን መጥፋት ከጀመሩ ሰነባብቷል፡፡ ታዲያ ማን ይመልስልኝ? የኔ ጭንቅላት እንደው ጥያቄ ሊመልስ ይቅርና የራሱንም መልስ መልሶ ለመጠየቅ ተስኖታል፡፡ አይ ትዕቢተኛው እኔ (በቁጭት) አይ በደለኛው እኔ ... ጽድቅ ልስራ ብዬ እንደገና ኃጥያት፣ (ትካዜ) ለነገሩ ምን ማድረግ ይቻላል! በምድር ላይ ነው የምኖረው፡፡ ስጋ እስካለኝ ድረስ ደግሞ የስጋዬንም ፍላጎት ማሟላት አለብኝ፡፡ አዎን ትክክል ባይሆንም ... ለጌዜውም ቢሆን እንዲህ እያልኩ ልጽናና፡፡ (አባ መቃርስን ሲመጡ አይቶ) አባ ... አባ (በማለት ጉልበታቸውን ስሞ ሰላምታ ያቀርባል፡፡)

አባ መቃርስ፡- እፎ ሀለውከ?

መነኩሴ፡- እግዚአብሔር ይሴባህ ወእፎአንተ?

አባ መቃርስ፡- እግዚአብሔር ይሴባህ፣

መነኩሴ፡- ለምንት መጻይከ ሀቤየ አባ?

አባ መቃርስ፡- መጻእኩ ሀቤከ ኦ ወልድየ ከመእትናበብ ምስሌከ በእንተ አሐዱ፡፡

መነኩሴ፡-(ከጥቂት ፋታ በኋላ) በሰላም ነው ፈልጌህ ነበር ያሉኝ አባ?

አባ መቃርስ፡- አዎን በሰላም ነው፡፡ እንዴት ነው? እየበረታህ ነው?

መነኩሴ፡- በጸሎትህ ብርታት እየጠነከርኩ ነው! ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እየተከናወኑልኝ ነው።

አባ መቃርስ፡- አሳቦችህ አይዋጉህም?

መነኩሴ፡- አሁን ደህና ነኝ አባ።

አባ መቃርስ፡- አየህ እኔ ለነዚህ ሁሉ ዓመታት በምንኩስና ኖሬያለሁ። ምንም እንኳን መነኩሴ ብሆንም የዝሙት መንፈስ እስካሁን ድረስ የፈታተነኛል።

መነኩሴ፡- እንደው አባቴ ሀፍረት ይዞኝ ነው እንጂ እኔንም ይፈታተነኛል።

አባ መቃርስ፡- በሱ ባቆም ጥሩ ይሩ ነበር! ብዙ ሰው ሲያወድሰኝ ሳይ ልቤ ይታበያል፣ ሌላውን እንደኃጥአተኛ ይቆጥራል።

መነኩሴ፡- አባ የኔ ኃጥያት ይብስ የለ መዋሸቱ፣ ወንድሞቸን መናቁ፣ ለስጋዬ መሳሳት፣ ምኑን ነግሬ ምኑን ልተወው? ስህተቴን ላለመድገም ስጥር ሌላ ስህተት ሌላ በደል አፈጽማለሁ።

አባ መቃርስ፡- ወዳጄ ሆይ በዚህ ምድር ላይ ብዙ ስህተት ልንሰራ እንችላለን፡፡ ይህንን ስህተት ግን ለንሰሐ አባታችን ተናግረን ንሰሐ ካልገባን ስህተቶችን ከሰውን ሰማያዊ ዋጋ ያሰጠናል፡፡ ያደፈ ገላችንን በውሃ እንደ ምናጸዳ ሁሉ ለኃጥያትና ለበደል ማጥፊያ ውሃው ንሰሐ ነው፡፡ ፈጠን ብለን ንሰሐ ካልገባን ግን ልክ ያደፈ ገላችን በበሽታ አምጭ ተውሳኮች እንደሚጠቃ የኃጥያትና የበደል ምንጩም ሆነ ምክንያት አምጭ ተወሳኩ ዲያቢሎስ ስለሆነ ወደ ክፉ መንገድ ይመራናል፡፡ እናም ወዳጄ! አንተም ለንሰሐ እነደዘገየህ ስለሰማሁ የሠርግ ቤቱ ከተዘጋ በኋላ ከሚያንኳኩት መሃል እንዳትሆን የአባትነቴን ልመክርህ ወደድሁ፡፡

መነኩሴ፡- ዲያቢሎስ ቀንና ሌሊት እየመጣ ቢያስጨንቀኝ የስጋ ፍላጎቴን አብዝቶ ቢፈትነኝ እኮ ነው ከእግዚአብሔር መንገድ የራቅሁት፡፡

አባ መቃርስ፡- አትሳሳት! የእግዚአብሔር መንገድ ከገቡባት ለስህተት የሚሆን መታጠፊያ እንኳን የላትም፡፡ በሷ ላይ ዲያቢሎስ የለም፡፡ ካልቀረብናት ግን ዲያቢሎስ ያጠምደናል፡፡ አሁን የሚበጀው ንሰሐ ገብቶ መመለሱ ነው፡፡ ነገ ዛሬ ሳትል አሁኑኑ ንሰሐ አባትህ ጋር ሂደህ ነገሩን ሁሉ በግልጽ አስረዳ፡፡

መነኩሴ፡- እሺ አባ፡፡ እንደውም አሁኑኑ እሄዳለሁ፡፡ (ብሎ ተከትሏቸው ይወጣል)

ትዕይንት ፫

አባ መቃርስ፡- (*መጋረጃ ሲከፈት አባ መቃርስ ብቻቸውን ይታያሉ*) አንተ እርኩስ መንፈስ አሁንስ በበረሀ ካሉት መነኮሳት ጋር ስራህ እንዴት ነው?

ሳጥናኤል፡- (በንዴት) አሁንም እጅግ በጣም በጣም መጥፎ ሆኗል፡፡ ወዳጄ ያልኩት መነኩሴ እንኳን ያሳሰብኩት ኃጥያት ሁሉ ለንሰሐ አባቱ እየነገረ ነው፡፡ ይባስ ብሎ እንደ በፊቱ እንዳላስጨንቀው ዘወትር በመስቀሉ እያማተበ መጠጋት አልቻልኩም፡፡

አባ መቃርስ፡- ዘወትር ስራዬ መጥፎ ይሁን፡፡ አንተ ሰው ጠላት ነህ ከሳሽ' ጋኔን የጨለማው ገዢ ፊታኝና ሌባ ነህ፡፡ የክፋት ሰራዊት የምትመራ እርኩስ መንፈስ የተጠናወተህ ዘንዶና የዚህ አለም ገዢ ባለጋራ ነህ ንሰሐን ስለማታውቅ ዘወትር ስራህ ከአምላክ ተቃራኒ ነው፡፡ አሁን ከአጠገቤ ራቅ፡፡ (ፋታ) ይህንን ያደረገ አምላክ ክብሩ የስፋ፡፡ ሰው ከሰይጣን ይርቅ ዘንድ ንሰሐ ይግባ፡፡ ጌታ ሆይ ክብር ምስጋና ዝማሬ ጸሎት እና አምልኮ ለአንተ የሚገባ እሰግድልሃለሁ (ተንበረከኩ) እነሆ ሰው የጠላት የዲያቢሎስ ወዳጅ እንዳይሆን ንሰሐ ይግባ፡፡ ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡(መሬቱን ሳሙ)

(የቅዱሱ አባታችን አባ መቃርስ አንድ የበረሃ አጋጣሚ ለድራማ እንዲመች ተደርጎ የተጻፈ)

ሕሊና በለጠ
ለቦ/ኖ/ብ/ቅ/ማ/ቤ/ሰ/ት/ቤት

በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ዓዲ-ሓቂ ግቢ-ጉባኤ በስነ-ጽሁፍ ንኡስ ክፍል ድጋሜ ተስተካክሎ የቀረበ።
ጥቅምት 2008